# *የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)*

*Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*


ሐሙስ ህዳር 11 ቀን 2007 ዓ.ም.

## *የታዳጊ ልጆች መብትን ማስከበርና መንከባከብ የሀገር ወዳዱ ግዴታ ነው!!*

የአንድ ሀገር ሕዝብ ታላቅነቱ የሚመዘነው በባዕድ ወራሪ የጭቆና ቀምበር ላለመውደቅና የሀገሩን ዳር ድንበር ለማስጠበቅ ባደረገው ወይንም በሚያደርገው ተጋድሎ ብቻ የሚመዘን እንዳይደለ በርካታ ተመክሮዎች የሚያመላክቱት ናቸው። ከዚህ ተጋድሎው ጋር በጥብቅ መያያዝ ያለበትና በተግባርም ሊረጋገጥ የሚገባው የሁሉም የሀገሪቷ ዜጎቹ በተለይም ደግሞ ታዳጊ ወጣቶች ሙሉ መብታቸው ያለምንም ገደብ ሕዝብ በትግሉ ማስከበር ሲቻለው እንደሆነም ተመክሮዎች የሚገልፁት ናቸው። በገሃድ እንደሚታየው የወደፊት ሀገር ተረካቢ የሆኑ ታዳጊ ልጆች በደል ሲደርስባቸው እድሜያቸው ከአቅመ አዳምና ሄዋን በላይ እንደሆኑት ራሳቸውን በአግባቡ ለመከላከል ስለማይቻላቸው ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ መስጠቱ ወሳኝነት ያለውና ሀገራዊ ግዴታ እንደሆነ የፀና እምነታችን ነው። ይህ ሲባል ደግሞ አለምክንያት አይደለም። መብቶቻቸው በማይከበርበት፡ በደል በበዛበትና ፍትህ በጎደለበት ሁናቴ የሚያድጉ ታዳጊ ወጣቶች በለጋ አዕምሯቸው ውስጥ የሚቀረፀው የሕሊና ስብራት ለሕብረተሰቡ ጤናማ እድገት እንቅፋት በመሆኑና ይህንንም ለማረም የሚያስፍልገው ወጪ በቀላሉ የሚገመት እንዳልሆነ በርካታ በርዕሱ ምርምር ያደረጉ የስነፍጡር ተመራማሪዎች የሚገልፁትና በተግባር እየታየ ያለ በመሆኑ ነው።

ይህንን እውነታ ከግምት በማስገባት ነበር ከዛሬ 100 አመት በፊት በ1924 አ.ም. በርካታ ሀገራት የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውሳኔ ለመወሰን መሰረት የሆነውን ረቂቅ ለመንደፍ የቻሉት። ይህ ሂደትም ፍሬ አስገኝቶ የዛሬ 25 አመት በ 1989 ዓ.ም. ከወቅቱ የግንዛቤ ሁኔታ ጋር በማዛመድ „ የታዳጊ ልጆችን መብት የሚያስጠብቅ የጄኔቫ ስምምነት“ የተባለውን ሰነድ በኖቬምበር 20 ቀን (ህዳር ll ቀን 2007 ዓ.ም.) ይፋ ለማድረግ፡ ይህም ቀን በየአመቱ እንዲከበር ለመወሰን የተቻለው። ይህም በ191 መንግሥታት ተቀባይነትን አግኝቶም ከተግባር ለማዋል ጥረት እየተደረገ የሚገኘው።

ይህ 54 አንቀጾችን የያዘ ስምምነት በውስጡ፡

- ታዳጊ ልጆችን ከብዝበዛና በደል መታደግ
- እኩልነትን ማስፈን
- እያንዳንዱ ልጅ ትምህርት የማግኘት መብት መከበር፡
- በቂ የእረፍትና የመዝናኛ ጊዜያት ማግኘት
- ሃሳብን በነፃ መግለፅና መደመጥ
- ከኃይል ጥቃት ነፃ የሆነ እድገት ማግኘት




**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email ESPIC@aol.com**
**Website WWW.EPRP.com**

**EPRP**
**BP 30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**

- ጤንነት የመጠበቅ
- በልጆች መካከል የፆታ ልዩነት አለማድረግ
- የወላጆች በቂ እንክብካቤ ማግኘት
- ከሃይል ጥቃት፡ ረሃብ፡ ጥማትና ከመታረዝ መታደግ የተሰኙት ይገኙበታል።

ይህ ይሁን እንጂ አሁንም በበርካታ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ታዳጊ ልጆች ከ 25 አመት በኋላም መጠነ ሰፊ የሆነ የኃይል ጥቃት፡ የፍትህ ጉድለትና ብዝበዛ ይደርስባቸዋል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ልጆች ማህበራዊ ቀውሶች በሰፈኑበት አካባቢ ለመኖር የተገደዱ ናቸው። በርካታዎች በጦርነትና በተፈጥሮ አደጋ ሳቢያ ሕይወታቸው ያልፋል። በየአስር ደቂቃው ወጣት ሴቶች በሚደርስባቸው የኃይል ጥቃትና የተለያዩ በደሎች ሕይወታቸው ያልፋል። የፆታ ልዩነት አሁንም በስፋት የሚንፀባረቅ ክስተት ነው።

በወያኔ አገዛዝ ሥር በምትማቅቀው ኢትዮጵያም ምንም እንኳ እንደ ሌሎቹ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሁሉ ለፕርፓጋንዳ ፍጆታ ሲባል የታዳጊ ልጆች መብቶችም ሕገ አገዛዜ በሚሉት ሰነድ የተካተቱና ነጋ ጠባ በካድሬዎቹ እየተነገሩ ቢገኙም የወላጆቻቸው መብት ያልተከበረ በመሆኑ የነሱም ከዚሁ ምደባ ሊያመልጥ አልተቻለውም። በረሃብ አለንጋ የሚረግፉት፡ በአስገድዶ መድፈርም ሆነ የተለያዩ በባሕል ተስታከው በታዳጊ ልጆች ላይ የሚደርሰው በደልና ግፍ አሁንም እንደቀጠለ ነው። በቅርቡ በአንዷት ታዳጊ ወጣት ላይ የደረሰው የአስገድዶ መድፍርና ለሞት መዳረግ በተመሳሳይ ሁናቴ በበርካታዎች ላይና  በጠቅላላ የሀገሪቷ አካባቢ እየተደረገ ያለ በጥብቅም የሚወገዝ ተግባር በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ነው።

በሕፃናትና በታዳጊ ልጆች ላይ የሚደርሰው ወሲባዊ ብዝበዛ በሚያስፈራ ሁኔታ እየተዛመተ ይገኛል። የልጆች መብት የሰብአዊ መብት አካል መሆናቸው ዛሬም በሚገባ ከግንዛቤ የገባ አይደለም። ድህነትና ረሃብ በተስፋፋበት፡ ንፁህ ውሃ እንደ ልብ በማይገኝበትና ብዝሁናኡ ሕዝባችን በሚኖርበት በገጠሩ አካባቢ በቅርቡ ይፋ በሆነ ዘገባ እንደተጠቆመው እርጉዞች ልጃቸውን የሚወልዱት አሁንም አግባብነት ያለው የሕክምና አገልግሎት በማግኘት አይደለም። ይህም በበኩሉ በቀላል ክትባት ሊወገዱ በሚችሉ በሽታዎች እየተጠቁ ለሞት የሚዳረጉት ወላጆችና ሕፃናት ቁጥራቸው በርካታ ነው። በትላልቅ ከተሞች ለመንገድ አዳሪነትና ለተለያዩ በቀላሉ ሊወገዱ በሚችሉ የበሽታ አደጋዎች እየተጠቁ ያሉ ታዳጊ ልጆች ቁጥራቸው በርካታ ነው። ያለ እድሜያቸው ለጋብቻ የሚዳረጉ፤ ሳይወዱ በግድ ጠለፋ የሚካሄድባቸው፡ የተመጣጠነ ምግብ ባለማግኘት የሚደርሰው የአዕምሮ ዕድገት መናጋትና አልፎ ተርፎም በሕፃናት ላይ እስከሞት በሚያደርስ በሽታ የሚጠቁት ቁጥራቸው በቀላሉ የሚገመት አይደለም።



**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email [ESPIC@aol.com](mailto:ESPIC@aol.com)**
**Website [WWW.EPRP.com](http://WWW.EPRP.com)**

**EPRP**
**BP 30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**

የታዳጊ ልጆች መብት የተወሰነበት ኖቬምበር 20 (ሕዳር ፲፩ ቀን 2007 ዓ.ም.) እንዳለፉት አመታት ሁሉ ዘንድሮም በአለም አቀፍ ደረጃ በሚከበርበት ጊዜ የታዳጊ ልጆች መብት እንዲከበር እየታገለ የሚገኘው ኢሕአፓ ይህ መብት ከወላጆቻቸውም ሆነ ባጠቃላይ ከሕዝቡ መብት መከበር ለይቶ የሚያየው ስላይደለ ይህ ሁናቴ እንዲቀጥል ያደረገውን የወያኔ አገዛዝን በጥብቅ ያወግዛል። በህቅ ያልተሞላ ፕሮፓጋንዳውንም እየኮነነ ሁኔታው እንዲቀየርም ዜጎች የተቻላቸውን ጥረት እንዲያደርጉም ጥሪውን ያስተላልፋል። የአዞ እንባ ማፍሰስ ሳይሆን በተግባር ከተበዳዮች ጎን መቆም እንድቀድሞው ሁሉ አሁንም ወቅታዊ ነው። ኢሕአፓም ይህንን ጥሪ ሲያስተላልፍ ፈንጠር ብሎ ዳር ቆሞ ሳይሆን ከተበዳዮቹ ከጎናቸው በመሰለፍ የበኩሉን አስተዋፅዖ የሚያበረክት መሆኑን ከመግለፅ ጋር ነው። ሆኖም የወላጆቻቸው መብት በተግባር እስከሚከበር ድረስ ወላጆችም ሆኑ ለሕዝብ ቅን አሳቢ ሀገር ወዳዶች ባላቸው አቅም ልጆቻቸውን ከተለያዩ ጉዳቶች እንዲጠብቁ ልባዊ ምክሩን አፅንዖት በተሞላበት መልክ ሳያሰልስ ጥሪውን ያስተላልፋል። ያስተምራልም። ትግሉ ስኬታማ ሊሆን የሚችለው በጋራ ጥረት ነውና ለዚህ መሰረት የሚሆነውን የሙብት መከበር ጥያቄ በማንገብ ዜጎች ከምንጊዜውም በላይ እንዲንቀሳቀሱና፡ የርስ በርስ መተሳሰብንና መረዳዳትን እንዲያጎለብቱም የከበረ አደራውንም ያስተላልፋል።

***ታዳጊ ወጣቶች መንከባከብ ሀገራዊ ኃላፊነት ነው!***



**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email [ESPIC@aol.com](mailto:ESPIC@aol.com)**
**Website [WWW.EPRP.com](http://WWW.EPRP.com)**

**EPRP**
**BP 30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**